***ከትብብር ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ 1999 ዓም የዘመን መለወጫ በሚመለከት ለኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ የተሰጠ መግለጫ፤***

1998 አብቅቶ 1999 እየመጣ ነው:: ከዳር እስከ ዳር ተነስተህ ለነጻነትህና ለዴሞክራሲያዊ መብትህ መከበር በ1997 ያሳየኸውን ቆራጥነት በ1998 አጠናክረህ ቀጥለህበታል:: የተያያዝከውን መራር ትግል ለ1999 ከፍጻሜ ለማድረስ ቆርጠህ ተነሳ::

ህዝብ አንድ ግዜ የነጻነት ደወል በህሊና ውስጥ ካቃጨለ ከአሰበው የነጻነት አምባ ሳይደርስ ሊገታው የሚችል ምንም ሃይል እንደሌለ የሃገሪቱ አምባገነን ገዥዎች አልተረዱም::

አንተ ሰላም ስትላቸው ጦርነትን፣ እርቅ ስትላቸው ጠብን፣ እኩልነት ስትላቸው አድልዖን፣ አንድነትን ስትላቸው መከፋፈልን እየመረጡልህ በባርነት እና በድህነት እንድትኖር አድርገውሃል::

በቃላት ማጭበርበሩ፣ በሃሰት ማወናበዱ እና ማሰሩ፣ ለመደለል መሞከሩ፣ አልፎ ተርፎ በባለመነጽር ጠምንጃ እያንጣጣሩ መግደሉ የህዝብን የነጻነት ሰልፍ እንደማያወላግደው ላላወቁ ገዥዎች የመጨረሻውን የጅምላ እልቂት ድግሳቸውን ደግሰው እርስ በእርስ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ተከፋፍለህ እንድትባላ አስበው ነበር:: በእዚህ ድግሳቸው አንተ እርስ በርስህ ስትባላ እነሱ እንደልማዳቸው «በእዚች ምድር ላይ ሰላም እና እርጋታ ያለእኛ ገዥነት ሊኖር አይችልምና ጸጥ ለጥ ብለህ ተገዛ» በማለት የተነቃነቀ የስልጣን ዙፋናቸውን አጥብቀው ሊፈነጩብህ አስልተው መንቀሳቀስ ላይ ናቸው:: አንተ ግን እርቆ አስተዋይ ነህና አምቢ አልካቸው:: ይህ የ1998 አንዱ ትልቅ ድል ነው::

ሌላው 1998 ለህዝብ የተወው በታሪክ የሚታወስ ድል «ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ» መመስረቱ ነው:: 1998 የወያኔን የእልቂት ሴራ ማክሸፍ የሚቻልበትን፣ ለአስተማማኝ ዴሞክራሲ እና እኩልነት፤ በእዚህም ላይ ለቆመ የህዝብ አንድነት መሰረት የተጣለበት ዘመን ሆኖ ሲታወስ ይኖራል:: በእዚህ ትብብር አማካይነት ወሽመጣቸው የተበጠሰው የወያኔ ኢህዴግ ባለስልጣናት አንዱን ብሄር ከሌላው ብሄር ጋር እንዲናከስ በማድረግ የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም አስልተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ::

በአዲሱ አመት ትብብሩ የገባውን ቃል ኪዳን በተግባር በማዋል የወያኔን ሴራ በማምከን ባጠቃላይ ፖለቲካ እስረኞች በሙሉ የሚፈቱበት፣ የተሰደዱት የሚመለሱበት፤ በግፍ ንጹሃንን የተገደሉ ለፍርድ የሚቀርቡበት የኢትዮጵያ ህዘብም በደሙ መስዋእትነት የከፈለለት የዴሞክረሲ እና የነጻነት ህልሙ እውን እንዲሆን ትግል የሚያደርግበት እንደሚሆን ጽኑ እምነታችን ነው::

አሁንም የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የገዥዎቻችንን እና የተከታዮቻቸውን መከራ እና ስቃይ ማሳጠሪያው መንገድ ትብብሩ የጠራውን የእርቅና የሰለማዊ ሽግግር መተለሚያ ሁሉን የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ፣ የሃይማኖት እንዲሁም ልዩ ልዩ የሙያ ዘርፍን ያሳተፈ ሃገራዊ ጉባኤ ማድረግ ብቻ ነው::

1999 በተባበሩት የነጻነት እና የዴሞክራሲ ሃይሎችና ትብበሩን በሚደግፈው የሃገሪቱ ሃዝብ ትግል ነጻነታችንን እና ዴሞክራሲያዊ መብታችንን የምንጎናጸፍበት እንዲሆን የትብብሩ አባል ድርጅቶች፣ አባላትና ደጋፊዎች መላው ሰላም ወዳድ የኢትዮጵያ ድርጅቶችና ግለሰቦች እጅ ለእጅ በመያያዝ ትግሉን በማፋጠን የወያኔን መሰሪ አለማ ለማምከን እንድትንቀሳቀሱ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

1999 የህዘብ የነጻነት የዴሞክራሲ የእኩልነት አንድነትና የሰላም ጥማቱ የሚረካበት ይሆናል:: መልካም አዲስ አመት::

ትብብር ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ

ጳጉሜ 2 ቀን 1998 ዓም